የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት የሚስተካከልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ቁጥር--------/2019

አዲስ አበባ፤

መስከረም፤ 2019 ዓ.ም

<u>መመሪያ ቁጥር … /2019</u>

"የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት የሚስተካከልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ"

የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው የስሌት ወይም የሂሳብ ስህተት በሚኖርበት ጊዜ፣በውሳኔ ወቅት ያልታየ አዲስ ወይም አግባብነት ያለው ማስረጃ ያላካተተ ከሆነ፣ውሳኔው ከአስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም በሚሆንበት ጊዜ እና በማስታወቂያው ላይ ያለው ስህተት በታክስ አወሳሰኑ ላይ የተሳሳተ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ማረም ተገቢ በመሆኑ፤

በታክስ አወሳሰን ወቅት ያልታየ አግባብነት ያለው ወይም አዲስ ማስረጃን መሰረት በማድረግ ስህተቶችን በማረም ፍትሐዊነትንና ግልጽነትን ማስፈን ስለሚያስፈልግ በተሻሻለው የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1434/2018 አንቀጽ 96(2) መሰረት ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

"የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት የሚስተካከልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር ...../2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ልላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከል"** ማለት በአዋጁ (እንደተሻሻለ) ከአንቀጽ 96 እስከ 102 በተጠቀሱት ድንጋጌዎች እና በዚህ መመሪያ መሰረት ማስተካከል ነው፡፡

2/ **"ስህተት ወይም ግድፈት"** ማለት የስሌት ስህተት፣የቁጥር መቀያየር፣የአመዘጋገብ ስህተት፣የቃላት አገባብ ስህተት፣ለስሌቱ የማይመለከተውን ወጪ ወይም ገቢ ማካተት ወይም መተው፣የሌላን ታክስ ከፋይ ሂሳብ መጨመር፣ማቀላቀል ወይም ማቀያየር፣የታክስ መጣኔ ወይም የትርፍ ህዳግ መሳሳት ሲሆን በታክስ አወሳሰን ወቅት ያልታየ አግባብነት ያለው ማስረጃ ወይም በአዋጁ መሰረት በሚቀርብ አዲስ ማስረጃ መሰረት የሚመጣን የስሌት ለውጥ እና አስገዳጅ ትርጉም ጋር ባለመጣጣም የሚመጣን ስህተት ይጨምራል፡፡

3/ **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም —⇔T⊥ϑ፡፡

4/ **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ሲሆን ማሻሻያውንም ይጨምራል፡፡

5/ በታክስ አሰተዳደር አዋጅ ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ከነማሻሻያው ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ ከነማሻሻያው የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

ክፍል ሁለት

የስህተት ማስተካከያ ምክንያቶችና ሁኔታዎች

3. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የማስተካከያ ምክንያቶች

የታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የደረሰውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያ ሊያደርግ የሚችለው፤

1/ የስሌት ወይም የሂሳብ ስህተት ሲኖር፤

2/ በታክስ አወሳሰን ወቅት ያልታየ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሲኖር፤

3/ በአዋጁ መሰረት የቀረበ አዲስ ማስረጃ ሲኖር፤ወይም

4/ የታክስ ውሳኔው አስገዳጅ ከሆነው የታክስ ህግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ሲሆን ነው፡፡

4. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያ ሁኔታዎች

የታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የደረሰውን የታክስ ውሳኔ ለማስተካከል የሚያበቁት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1/ ስህተቱ መሰረታዊ ሆኖ ታክስ የመክፈል ግዴታን ወይም ታክስ ተመላሽን የሚያስከትል ውጤት የሚኖረው ሲሆን፣

2/ የስህተት ማስተካከያው ሊረጋገጥ በሚችል መረጃ ወይም ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ ወይም

3/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማስረጃው መቅረብ ካልቻለ ወይም አዲስ ማስረጃ በመገኘቱ ካልሆነ በስተቀር ስህተቱ እንዲታረም ጥያቄው ለታክስ ባለስልጣኑ የቀረበው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ከሆነ ነው፡፡

ክፍል ሦስት

የጊዜ ገደብ

5. ስህተት የማስተካከያ ይርጋ ጊዜ

1/ ስህተት የማረም ሂደት የሚጀምረው በታክስ ከፋዩ ስህተት ይታረምልኝ የሚል ማመልከቻ ሲቀርብ ወይም የታክስ ባለስልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ስህተት መኖሩን ሲያምንበት ነው፡፡

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(3) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የታክስ ባለስልጣኑ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው፤

(ሀ) የመጀመሪያው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ዓመታት ውስጥ፤ ወይም

(ለ) ስህተቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በ1 (አንድ) ዓመት ወስጥ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ 2 (ሀ) ወይም (ለ) በቀደመው ጊዜ ማስተካከያው ሲደረግ ነው፡፡

ክፍል አራት

የአሰራር ሂደት

6. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚስተካከልበት የአሰራር ሂደት

1/ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የተከሰተ ስህተት ከዚህ በታች እንደሚከተለው የሚታረም ይሆናል፡፡

ሀ) የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ስህተት አለበት የሚል ታክስ ከፋይ ውሳኔውን ለሰጠው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥያቄውን በፅሑፍ በማቅረብ ስህተቱ እንዲታረምለት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ለ) የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያውን የሰጠው የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ ክፍል በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሲመራለት በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የተፈፀመ ስህተት መኖር አለመኖሩን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

ሐ) ሥራ አስኪያጁ የቀረበውን ማስረጃና የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ በቅ/ፅ/ቤት ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

መ) ስህተቱ ተጣርቶ የቀረበለት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ጉዳዩ በታክስ ከፋዩ የማስረጃ አቀራረብ መዘግየት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ስህተት ይታረምልኝ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ሠ) የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሊታረም የሚችል ስህተት አለመኖሩን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ እና ታክስ ከፋዩ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ያለው ከሆነ ውሳኔው በደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ፡-

1) በታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ሥር ባለ የሥራ ክፍል የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ፣ ወይም

2) በታክስ ሥርዓት ዘርፍ ሥር ባለ የሥራ ክፍል የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለታክስ ሥርዓት ዘርፍ፣

አቤቱታውን ያቀርባል፡፡

ረ) ጉዳዩን የማየት ኃላፊነት ያለበት ዘርፍ በታክስ ከፋዩ የማስረጃ አቀራረብ መዘግየት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ጥያቄውን መርምሮ ቢበዛ በአምስት የሥራ ቀናት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ሰ) በዘርፍ ደረጃ በተሰጠው ውሳኔ ያልረካ ታክስ ከፋይ ውሳኔው በደረሰው በሦስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ ሚኒስትር ያቀርባል፡፡

2/ በዚህ መመሪያ መሠረት ስህተት እንዲታረም ከተወሰነ በውሳኔው መሰረት የተስተካከለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል፡፡

3/ ለታክስ ከፋይ ተስተካክሎ የሚሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቀደም ሲል የተሰጠው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የተሻረ መሆኑን የሚገልጽና ስህተቱ በታረመበት ጊዜ ያለውን ቀንና ቁጥር የያዘ መሆን አለበት፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

7. <u>የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለማስተካከል ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ</u>

1/ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት እንዲታረምለት አቤቱታ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፡-

ሀ/ በታክስ አስተዳደር አዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን በፅሁፍ ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት፤

ለ/ ስህተት የተፈፀመበትን የውሳኔ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፤

ሐ/የስህተቱን አይነትና ምክንያት በግልፅ መገለፅ አለበት፤

መ/ ሌሎች ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ማቀረብ አለበት፤

2/ ስህተቱ እንዲታረም የሚቀርብ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት ያልቀረበ መሆን አለበት፡፡

3/ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ስህተት እንዲታረም አቤቱታ ማቅረቡ በታክስ አስተዳደሩ የተቀመጠውን አቤቱታ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ የሚያስቀር አይሆንም፡፡

4/ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ስህተት እንዲታረም አቤቱታ ማቅረቡ ሌሎች የታክስ ግዴታዎችን ማስፈፀምን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

8. <u>የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስለማሳወቅ</u>

1/የታክሱ ባለስልጣን የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መላክ አለበት፡-

ሀ) የስህተቱን አይነት፤

ለ) የማስተካከያውን ምክንያት፤

ሐ) በማስተካከያው ምክንያት ሊከፈል የሚገባውን ወይም ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን እና

መ) ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለመቃወም ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ያለውን መብት፡፡

9. <u>የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያ የሚኖረው ውጤት</u>

1/የሚዘጋጀው የተስተካከለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ፡-

ሀ/በተደረገው ማስተካከያ ልክ የመጀመሪያውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚተካ ይሆናል፤

ለ) የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ እንደተሰጠ ይቆጠራል።

2/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ በተሻሻለው የታክስ አስተዳደር አዋጅ ላይ ቅሬታ ለማቅረብ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የመጀመሪያው የውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

10. <u>በተደጋጋሚ ማስተካከያ በማድረግ ላይ የተጣለ ገደብ</u>

ማናቸውም የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በአንድ አይነት ስህተት ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ማስተካከያ ሊደረግበት አይችልም።

11. <u>የተሻሩ የአሰራር ስርዓት</u>

መመሪያ 152/2011 አንቀፅ 37፣*መመሪያ* 138/2011 አንቀፅ 14 እና 15፣*መመሪያ* 176/2015 አንቀፅ 30(2) በዚህ *መመሪያ* ተሽሯል፡፡

12. <u>*መመሪያው* የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ *መመሪያ* በሚኒስቴሩ ጸድቆ በሚኒስቴሩ እና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ፤ኢትዮጵያ

*መ*ስከረም፣2019 ዓ.ም

ዓይናለም ንጉሴ ዓሊ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር